# የውባንቺ ቢሻውና የአዜብ መስፍን የስልክ ወግ (ክፍል 2)

ከጥቂት ዓመታት በፊት የቀድሞው የኢትዮጵያ መንግስት ፕሬዘዳንት የኮ/ሌ መንግስቱ ባለቤት ወ/ሮ ውባንቺ ቢሻው ከወያኔው ጠ/ሚ ባለቤት ከአዜብ መስፍን ጋር ያደረጉት http://quatero.net/pdf/azeb-wubanchi.pdf በዚሁ በቋጠሮ ገጽ በጽሁፍ ቀርቦ እንደነበር ያነበባችሁ ታስታውሳላችሁ። በዛን ግዜ ወ/ሮ ውባንቺ ቢሻው ለእንጦጦ ማሪያም የተሳሉትን አንድ ኪሎ ወርቅ ለማስገባት ወደ ኢትዮጵያ ለመሄድ አስበው ስለነበር፡ ወያኔ እንደማያስሯቸው ዋስትና ለማግኘት ነበር ወ/ሮ አዜብ ጋር የደወሉት። ያገኙት ምላሽም ወርቁን መቀሌ ማሪያም ማስገባት አለብሽ የሚል ነበርና ወ/ሮ ውባንቺም ያልተሳልኩበት አላስገባም ብለው ሁሉም በዚሁ ተዘጋ። ዛሬም በሁለቱ ተቀዳሚ እመቤቶች መካከል የስልክ ውይይት ተደርጓል፡፡ ዛሬ ግን ጉዳይ አጋጥሟት የደወለቺው አዜብ ነች። ምን ይሆን የአዜብ ጉዳዩ? አብረን እንከታተል፡-

**አዜብ፡**-- ሃሎ ሃሎ ይሰማል!---

***ሃራሬ፡*** ይሰማል ማን ልበል? (የኮ/ሌ መንግስቱ ጎርናና ድምጽ ነበር)

**አዜብ፡**-- እዋይ! አምባገነኑ አነሣው! አዜብ ነኝ፤ ብናይ ኢትዮጵያ ቀዳማይ እመቤት አዜብ መስፍን!

***መንጌ፡*** ምን? ቀዳማይ ማ? ምን ፈልገሽ ነው? ለመሆኑ ይህን ስልክ ማን ሰጠሽ? አንቺ ወንበዴ የወንበዴ ....!

**አዜብ** ዋይ...! ዛሬም ይፈክራል ሰውየው? አተ! ተበገስ! የሸሸ አይፈክርም፡ ቁጥሩ ማሰጠሽ ላልከው ምሽትህን ጠይቅ ፤ ይልቅ ውባንቺ አቅርብልኝ ልዛረባት ?"

***መንጌ፡*** ሚስትህን ጠይቃት? እሷ ነች የሰጠችሽ? ሲ አይ ኤ እሷንም ጠልፎልኛላ? ስልጣኔን ብቻ መስሎኝ! ውባንቺ! ወባንቺ! ነይ ወዲህ ብለው ተጣሩ። (አዜብ እንዳትሰማ ስልኩን በመዳፋቸው ሸፍነው )

**ውባንቺ** -- አቤት ምን አለሁ "

***መንጌ፡*** -- ለመሆኑ ከዚህች ወንበዴ ጋር ምን ስትዶልቱልኝ ቆያችሁ? አንቺም ውባኒቺ..? አንቺም..?

**ውባንቺ** " እንደሱ አይደለም! ጓ/ሊ መንበር እውነት! እውነት! ዱለታ አይደለም። ያኔ አንተን ከሞት ካተረፈልኝ አንድ ኪሎ ወርቅ ለእንጦጦ ማሪያም ተስዬ ፡ ስለቱን ለማስገባት ለመሄድ በፈለኩበት ግዜ ነበር የደወልኩላት፡፤ ቁጥሩን ከዛ ነው ያገኘቺው"(በፍርሃት እየተንቀጠቀጠች)

***መንጌ፡*** እና ምን አለችሽ ታዲያ? ለምንድነው ያልነገርሽኝ? ደግሞ ቀዳማይ እመቤት ትበለኝ? የቀደመ ጅብ ይብላትና...! ይህቺ ዱር በቀል! ዘላን ወንበዴ ...በምንትዋብ ...!.በጣይቱ..! በዘውዲቱ...! በመነን... !ዙፋን ትዘፍዘፍ!(ኢይናቸውን እያጉረጠረጡ)

**ውባንቺ** " እንዴ ነግሬህ ነበር እኮ ረሳህው ?! እንዲያውም አብዮታችን ብዙ የበደለው የአራት ኪሎውን ቅድስ ሥላሴ ነው! ስለትሽን ለሱ ስጭ ብለህ ነበር እኮ በዛኑ ሰሞን አንድ ማታ ነግሬህ ?

**መንጌ:** እምምምም ይሆናል! ማታ ላይ ነው የነገርሽኝ ይሆናል! በይ እንኪ አናግሪያት ብለው (ከንዴታቸው በረድ ባለ መንፈስ ስልኩን አቀበሏት)

**ውባንቺ** " ሃሎ ውባንቺ ነኝ"

**አዜብ** " ሃሎ ውባንቺ  እንደምነሽ ? ዋይ ! ባልሽ ተቆጣ ኮ ምነው? ወንበዴ ፤ ምናምን አለ...ዛሬም ይፈክራል! "።የሸሸ አይፈክርም ተበገስ አልኩታ! ላ!ላ! !

**ውባንቺ** " ታዲያ ማን እንዲልሽ ፈለግሽ? ወንበዴ አይደለሽ እንዴ? ቀዳማይ እመቤት እንዲልሽ ነው?ቂቂቂ እመቤትነት እኮ በትግል አይገኝም...አዜብ ጎላ! ለመሆኑ ምን ፈለገሽ ነው የደወልሺው?

**አዜብ** " ዋይ! አሁንም ምላስ ብቻ ነሽ? ባልሽ ፍከራ አንቺ ምላስ .... "

**ውባንቺ** " አሁን ለምን ደወልሽ ንገሪኝ ምን ቀረሽ ደግሞ... ?"

**አዜብ** "እሺ እሺ አሁን የደወልኩት በቁም ነገር ነው"

**ውባንቺ** " ዘራፊ ቁምነገር አያውቅም ይልቅ ጉዳይሽን ተናገሪ ፤ "

**አዜብ** " ዋይ! ዛሬም እንደ ድሮ ነው የምታስቢኝ? ዛሬ እኮ ባለ ዲግሪ ነኝ!

**ውባንቺ** " ዲግሪ ነው ያልሽው? አንቺ ባለዲግሪ ? ቅቅቅ ሲሰጡሽ ስም አሳስተው ነው "ድግር" ለማለት ፈልገው ይመስለኛል። ድግርማ ድሮም ያንቺው ነው ......ቅቅቅቅ

**አዜብ** " ላ!...ይህቺ ሴት ምን ትላለች። ከማናጅመንት ኢኒስትቲዊት መመረቄ አላምንም ነው የምትዪው? የዲግሪዬ  ፎቶ ኮፒ  ልላክልሽ?

**ውባንቺ** " ኦርጅናሉን ድግር አውቀዋለሁ አትድከሚ......አትላኪ ቂቂቅ"

**አዜብ** " እዋይ ! ለሆነሬ እየሰራሁ ነው ባይገርምሽ...ምን ትሆኚ"

**ውባንቺ** " ለሞፈሬ ነው ያልሽው ? ጥሩ ስሪ ስሪ...በርቺ! ይልቅ አሁን ምን እንደፈለግሽ ንገሪኝ ! ስልኩ ይፈለጋል።

**አዜብ** " እዋይ ! ቁምነገሩ ፊዝ አርገሽ እንዴት ላስረዳሽ? !

**ውባንቺ** " ቁምነገሩን ተይና የደወልሽበትን አውሪ ! ተተርተሪ..እንዳልል ኢትዮጵያዊ ጨዋነቴ ያግደኛል !

**አዜብ** " ሆሆ..ምላስ እሳት!!! በይ ልንገርሽ፦ ጉዳዩ ለሁላችንም የሚጠቅም ነው፡! እንደሰማነው ሙጋቤ ዳይመንዳቸውን እንዳይሸጡ እገዳ ተጥሎባቸዋል። እና ህጋዊ በሆነ መንገድ መሸጥ ስለማይችሉ ለኤፈርት በቅናሽ እንዲሸጡ አንቺ እንድታግባቢያቸው ነው፡ ላንቺም ኤፈርት ያስብልሻል? ምን ይመስልሻል?

**ውባንቺ** " ቂቂቂ  ወደ ዝምባዌ ማነፍነፍ የያዛችሁት  የአዶላው አለቀ እንዴ? ዳይመንድ አልሽ? ኤፈርት በቅናሽ እንዲገዛ ከዝምባዌ ላይ እኔ ሙጋቤን ላግባባ? እናንተ ሰዎች እስካሁን የዘረፋችሁት አይበቃም? ሳትበሉ ለምትሞቱት ለምን ይህን ያህል ትንገበገባላችሁ

**አዜብ** " እዋይ ! ይቺ ሴት! ይሄ ቢዝነስ ነው መንገብገብ አይደለም! ባልሽ ኢኮኖሚስት አይደል ለምን አይነግርሽም! ግሎባላይዜሽን ሲባል አልሰማሽም? ዛሬ ማንም የትም ሄዶ መነገድ ይችላል።ኤፈርትም ይነግዳል...በቃ፡፤ አሁን በኔ ማናጅመት ስር ነው ኤፈርት አልሰማሽም? ይልቅ ሙጋቤ አናግረሽ መልሱ መቼ ትነግሪኛለሽ? "

ውባንቺ " የዝምባዌ ዳይመንድ ለምን እንደታገደ አልሰማሽም? ዳይመንዱ የደም ዳይመንድ ነው! ተብሎ ነው!

አዜብ " ዜናው ሰምቻለሁ። የደም ሆነ.. የአጥንት.. ሆነ ለኔ ምናገባኝ ? ለኔ የምፈልገው በቅናሽ እንዲሸጥ ነው።

ውባንቺ " አ ! ረስቼው ነው ደም ለካ የናንተ Favorite ምግብ ነው? ለትግራይ ርሃብተኛ የመጣ ዕርዳታ የዘረፋችሁ ለዝምባዌ ልትራሩ ነው?

አዜብ " ሌላ ሌላ ተይና ቢዝነስ አውሪ....ሙጋቤ ዳይመንድ መሸጥ ይፈልጋል፤ እኔ መግዛት እፈልጋለሁ።በቃ!

ውባንቺ " አንቺ ራስሽ ለምን አትጠይቂያቸውም?

አዜብ " ዋ! እኔማ ቀዳማይ እመቤት ነኝ! ደሞ አንዱ ጋዜጠኛ ቢሰማ ቅሌት ነው! ለመለስም ለ ኢ ህ አ ዴ ግ ም ቅሌት ነው!

ውባንቺ " ታዲያ ለቅሌት አዲስ አይደላችሁ! እንግዴ ልጃችሁ ቅሌት አይደል እንዴ ?"

አዜብ " ዋይ! ገና ለገና ቢዝነስ ታሰሪኛለሽ ብየ ልክ ልኬ ነገርሽኝ አንቺ ሴት! መታገሴ አይረዳሽም? "

ውባንቺ " ለመስረቅና ለመዝረፍማ ትግስተኞች ናችሁ...ለመግደል እንጂ ከአይን የምትቀድሙ "

አዜብ " ሆይ! ሙጋቤ ትዛረቢያለሽ ወይስ አትዛረቢም? ውባንቺ ሙች! ካናገርሽልኝ፡- የባልሽም ፍርድ አሰርዛለሁ

ውባንቺ " ክብር ፍርድ ቤቱም ፍርዱን የሚያነሳበት ጥቂት ዳይመድ ይደርሰዋል ማለት ነው?

አዜብ " ዋይ! የምን ዳይመንድ አመጣሽ ፤ ለፍርድ ቤቱ የ50 ሳንቲም ስልክ ይበቃል ። የዳይመንድ ሽያጭ ለኔና ላንቺ ነው?

ውባንቺ " እሺ ብልስ ምን ያህል ልትከፍይኝ ነው? "

አዜብ " እሱ ተይው በኔ!

ውባንቺ " እስኪ አስብበታለሁ! እስከዛው ስለ ምርጫው አውሪኝ ....

አዜብ " ጎሽ !አሁን ሃሳቤ ተረዳሽ! ምርጫማ ሰምተሻል ተቃዋሚ ሁሉ በዝረራ ማሸነፋችን!

ውባንቺ " አዎ 99.6 % ህዝብ መረጠን አላችሁ! 0.4% ሕዝብ ለምን ሳይመርጣችሁ ቀረ?

አዜብ " 0.4% ቱም ህዝብ ይመርጠን ነበር ያ ምላሰኛ መራራ አሉት እውነትም መራራ! አታሎት ነው!ዛሬ ግን ማታለል አይችልም ለመለስ አስወጣው ከምክር ቤት!

ውባንቺ " ቂቂቂ.. መለስ ነው እንዴ የምክር ቤት አባላት የሚመርጠው?

አዜብ " እዋይ ! ይቺ ሴት! ለመለስ ይምራን ብሎ የመረጠው ሕዝብ ማለቴ ነው አይረዳሽም። ካልተረዳሽ ዘፈንም ተዘፍኖለታል። ለመለስ ይምራን! ለመለስ ይቀጥል! ብሎ ድሮ ትምክህተኞች ያሳሳቱት ዘማሪ ዘፈነለት አልሰማሽም?

ውባንቺ " እረ ሰምቻለሁ! ሰሎሞን ተካልኝ የዘፈነውን አይደል?

አዜብ ለተካልኝ ነው? እንኟ ስሙ አልያዝኩትም፤ አንድ ቀን ግብዣ ላይ ለመለስ የዘፈነው ይሄ ነው ብሎ አንድ ትልቅ ድቡልቡል ዘማሪ!! አሳይተውኛል።

ውባንቺ " የቅንድቡ ብዛት፤ የቅድቡ ማማር....እያለ የዘፈነው አይደል ?

**አዜብ** " እዋይ! አሳሳቾች ጋር አትዋይ! የዘማሪው ጭብጥ  ቅንድቡ አይደለም :: ጭብጡ ለመለስ የልማት መሪ፤ የዕድገት መሪ ነው!

ይቀጥል ነው፤ ያለው። ቅንድቡ ጭብጥ አይደለም።

**ውባንቺ** "  ቅንድቡ አይጨበጥም ነው ያለሽው? ይጨበጣል እንጂ! ለምን አይጨበጥ? ኤፈርት ባይወጥርሽ እረ ብትነካኩኚውም

የሚነካነካን ይመስለኛል።

**አዜብ**   ዋይ! ነገርሽ ዘለፋ ሆነ በቃ! ተበገሽ

**ውባንቺ** "  እሺ እሱ ይቅር ተይው! ይልቅ ታምራት ጠንቋዩ ጋ እየሄድሽ ትከድሚ ነበር ሲባል የሰማሁት እውነት ነው?

**አዜብ**   የቱ ታምራት?  እዋይ! እኔ እንኳ እሱ ልከድም ለመለስም ከድሜ አላውቅ ግዜ የለኝም ! ኤፈርት አስተዳድራለሁ አላልኩሽም?

**ውባንቺ** " ኦ ! ረስቼው ነው። የመለስ ከዳሚዎች ለካ ወንዶች ናቸው....

**አዜብ** " ደሞ ማነው እንደሱ ያለሽ?

**ውባንቺ** " ሰምቻለሁ :- ኢስኒንን! በአማራ ላይ ሲቃም አዲሱ እንደሚከድም :-ከሚስን! :- በኦሮሞ ላይ ሲቃም አባዱላ

እንደሚከድም፡ ጁማአ ደግሞ:- በደቡብና በሱማሌው ሕዝብ ላይ ሲቃም፡ ተሾመ ቶጋ! እንደሚከድም፡ ሰምቻለሁ።

**አዜብ** " ላ! አዜብ ጎላ! አንቺ ሴት ቋንቋሽ ሁሉ አልረዳኝ አለ! ኢሲ፡ ጁማ፤ ከምሲ ምንድነው? ጸረ ሕዝብ ሚዲያዎችን ታዘወትሪያለሽ

መሰለኝ ንግግርሽ ከፋ....

**ውባንቺ** " ጸረ ሕዝብ ሚዲያ የትኞቹ ናቸው? እስኪ ነገሪኝ እንዳላያቸው፤ እንዳልሰማቸው ?

**አዜብ** " ታውቂያቸዋለሽ ከሬዲዮ እነ ቪ ኦ ኤ፤ ጀርመን፤ ከድረ-ገጾችም ብዙ ናቸው

**ውባንቺ** " ኢ ሣ ት የተባለውስ አሁን የተጀመረው የቴሌቪዥን ስርጭት ?

**አዜብ** " እዋይ ! እሱማ ዋናው አይደል! የኤፈርትን ገንዘብ የጨረሰ!

**ውባንቺ** " ኢ ሣ ት የኤፈርት ነው እንዴ?

**አዜብ**   እዋይ! ዋናው ጸረ ሕዝብ እሱ ነው እያልኩሽ ኢ ሣ ት ለኤፈርት ነው ወይ? ትይኛለሽ። ስርጭቱን ለመበገስ ከኤፈርት ካዝና

ብዙ ብር አስወጣ ነው የምልሽ። ምን የማይረዳት ሴት ነች ...!

**ውባንቺ** " የኤፈርት ካዝና እየጎደለ ስለሆነ ነዋ! በደም ዳይመንድ ሊሞላ ችኮላው?

**አዜብ** " ደሞ ተነሳባት ይህቺ ሴት.. የዳይመንዱ ጉዳይማ ዘጋነው...በቃ! አታደፍርሺ ነገር እዋይ!

**ውባንቺ** "  እረ ለመሆኑ ኤፈርትን የሚያስተዳድረው ! አቦይ ስብሃት አልነበረ እንዴ ለምን ተሻረ?

**አዜብ**   ምሽት ምሽት ብዙ የጠጣል! በቃ! አረጀ! ይዘባርቃል..ለሚጠጣ ሰው ለሚስጥር ሥራ አይኮነን..!በይ በቃሽ እንግዲህ

ለዳይመንዱ ጉዳይ! አደራ በሚስጥር ያዢውና ስትጨርሺ ደውይልኝ።

**ውባንቺ** " ሙጋቤ ቢሽጥላችሁ ለመሆኑ በምን ልትወስዱት ነው?

**አዜብ** " እሱን ለኔ ተይው! ዝምባዌ ኤንባሲ ውስጥ ካሉት ሰራተኞች አንዱ ድንገተኛ ሞት ይሞትና ከሱ ሬሳ ጋር ሊመጣ  ይችላል።

**ውባንቺ** " ደሞስ አንቺ ጋ ስደውልስ መለስ ቢያነሳስ?

**አዜብ** ሽግር የለም! እሱ ነው ደውይላት ያለኝ፤ ያውቃል ጉዳዩን...

**ውባንቺ** " ቅቅቅቅ ጠ/ሚሩ ናቸው ደውይ ያሉሽ ? ቅቅቅቅቅቅ በይ! በይ! ተይው ቅቅቅቅ፣ ለመሆኑ እስካሁን ያወራነው ሁሉ መቀዳቱን

አልጠረጠርሽም?

**አዜብ** " ለምን ትቀጃያለሽ?

**ውባንቺ** " ለኢ ሣ ት ልልከው ነዋ! ላሰማሽ እንዴ..ስሚው (ብላ የተቀዳውን አሰማቻት)

**አዜብ** " እዋይ! አበድሽ እንዴ? እረ ባክሽ ተይ እዋይ! ኢ ሣ ት ምን ይሰጥሻል....? ተይ ክፉ አትሁኚ! ዋይ! ውባንቺ ሙቺ የፈለግሺው

እሰጥሻለሁ ! ሃሎ ! ሃሎ!!!!!!

**ውባንቺ** " ቂቂቂቂቂቂቂቂቂ በይ ደህና ሰንብቺ ሊበላ አዜብ ጎላ! (ብላ እየሳቀች ስልኩን ዘጋቺው)

**አዜብ** " ጥርስሽ ይርገፍ ዋይ! ለኢ ሣ ት ልልከው አልች እ ሣ ት ይብላሽ! አቡነአረጋይ እሳት ይጨምሩሽ! ዋይ! ይህቺ ሴት ጉድ ሰራችኝ!

አሁን ቶሎ ለመለስ ነግሬ ለሚከድ ጥብጣብ ያዘጋጅ! እዋይ! ቅሌት...